የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፴፫
አዲስ አበባ ሰኔ ፳፪ ቀን ፲፱፻፺፰

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

12th Year No. 33
ADDIS ABABA 29th June, 2006

<u>ማውጫ</u>

አዋጅ ቁጥር ፬፻፺፯/፲፱፻፺፰ ዓ.ም
ለወሊሶ አካባቢ የገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል ብድር ከአረብ ባንክ ለአፍሪካ ኢኮኖሚ ልማት ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ... ገጽ ፫ሺ፬፻፴፫

## አዋጅ ቁጥር ፬፻፺፯/፲፱፻፺፰ ዓ.ም

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአረብ ባንክ ለአፍሪካ ኢኮኖሚ ልማት መካከል የተደረገውን <u>የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ</u>

ለወሊሶ አካባቢ የገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል መጠኑ ፫ ሚሊዮን ፮ መቶ ሺህ የአሜሪካን ዶላር /ሦስት ሚሊዮን ስድስት መቶ ሺህ የአሜሪካን ዶላር/ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአረብ ባንክ ለአፍሪካ ኢኮኖሚ ልማት መካከል እ.ኤ.አ. ማርች ፭ ቀን ፪ሺ፮ የተፈረመ በመሆኑ፣

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፩ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፣

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ /፩/ እና /፲፪/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል::

### ፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "ለወሊሶ አካባቢ የገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከአረብ ባንክ ለአፍሪካ ኢኮኖሚ ልማት ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፬፻፺፯/፲፱፻፺፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

<u>CONTENTS</u>

**Proclamation No. 497/2006**

Arab Bank for Economic Development in Africa Loan Agreement for Financing Rural Electrification Project in Wolliso Area Ratification Proclamation…. Page 3433

## PROCLAMATION NO. 497/2006.

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE ARAB BANK FOR ECONOMIC DEVELOPMENT IN AFRICA

**WHEREAS,** a Loan Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Arab Bank for Economic Development in Africa stipulating that the Arab Bank for Economic Development in Africa provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan amount of USD 3,600,000 (three million six hundred thousand United States Dollars) for financing Rural Electrification Project in Wolliso Area was signed on the 5th day of March 2006;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 8th day of June, 2006;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 Sub-Article (1) and (12) of the Constitution it is hereby proclaimed as follows:

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Arab Bank for Economic Development in Africa Loan Agreement for Financing Rural Electrification Project in Wolliso Area Ratification Proclamation No. 497/2006."

**፪. <u>የስምምነቱ መፅደቅ</u>**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአረብ ባንክ ለአፍሪካ ኢኮኖሚ ልማት መካከል እ.ኤ.አ. ማርች ፭ ቀን ፪ሺ፮ የተፈረመው የብድር ስምምነት ፀድቋል::

**፫. <u>የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ ሥልጣን</u>**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፫ሚሊዮን፮መቶሺህ የአሜሪካን ዶላር /ሦስት ሚሊዮን ስድስት መቶ ሺህ የአሜሪካን ዶላር/ በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል::

**፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል::

አዲስ አበባ ሰኔ ፳፪ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም.

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**2. Ratification of the Agreement**

The Loan Agreement signed between the Federal democratic Republic of Ethiopia and the Arab Bank for Economic Development in Africa on the 5th day of March 2006 is ratified;

**3. Power of the Minister of Finance and Economic Development**

The Minister of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the loan amount of USD 3,6000,000 (three million six hundred thousand United State Dollars) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

**4. Effective Date**

This Proclamation shall enter into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 29th day of June, 2006**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት